## በጉባኤና ድጋፍ ሰልፍ አዘጋጅ ግብረ ሃይል ስም ባስቸኳይ የሚወጣ መግለጫ ሃሳብ

# የሰበርነው የጥፋት አዙሪት መልሶ እንዳይገጥም

### ወይም ደግሞ አማራጭ አርእስት

# ድምፃችን እንዳይሰረቅ! ድላችን እንዳይቀለበስ!

የኢትዮጵያ ህብረተሰብ አንዴ በገዥዎች የጥቅም ግጭት፤ ሌላ ጊዜ በብሄሮችና በጠቅላላው ህዝብ የህልውናና የመብት ተጋድሎ፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ የውጭ ወረራዎችን ጥቃት ለመቋቋም በተከታታይ በተካሄዱ የክብርና የብሄራዊ ነፃነት ትንንቆች የተነሳ ባልተቋረጡ የጦር ግጭቶች ለዘመናት ሲዋከብ የኖረ ህብረተሰብ ነው። በዚህ ጊዜና ታሪክ ተጋግዘው በጎዱት ህብረተሰባችን ውስጥ ኢትዮጵያውያን በሙሉ የሰላም ፋታ፤ የዴሞክራሲና የማህበራዊ ፍትህ ፍንጭ ተነስተው ለዘመናት በመቆየታቸው ሃገራችን የርሃብ፤ የስደት፤ የኋላ ቀርነትና የጭቆና ቋት ሆና እንደቀረች ለሁላችንም ግልፅ ነው። ድህነት፤ የዴሞክራሲ መጥፋት፤ መራቆትና የማህበራዊ ፍትህ መጓደል የሚቀሰቅሷቸው ግጭቶች መልሰው ድህነታችንንና ጭቆናን እያባባሱ፤ የማህበራዊ ፍትህን ደብዛ እያጠፉ ይህ ደግሞ በተራው ሁኔታዎችን ለሌሎች ግጭቶችና ጦርነቶች እያመቻቸ ህብረተሰባችንን እንደዚህ አውተብ-ትበው እጅ ከወርች ካሰሩት የጥፋት አዙሪቶች ለመላቀቅ የሚያስፈልገውን ፋታ ሳያገኝ ለዘመናት ቆይቷል።

የእነዚህ የጥፋት አዙሪቶች መከማቸት ጠንቅ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ድቀታችን ብቻ አይደለም። በፖለቲካው መስክ አመፅን እንደመደበኛና የመጀመሪያ አማራጭ የልዩነት መፍቻ መሳሪያ አድርጎ የሚያይ አስከፊ ባህል በህብረተሰባችን ሰርፆ እንዲገባ አድርጓል። በሃገሪቱ ለሚከሰቱ የፖለቲካ ልዩነቶች ሁሉ አማራጭና አስታራቂ መፍትሄ ሳይፈልጉ የመሳሪያ ግጭትን መጋበዝ፤ የፖለቲካ ተቃዋሚን ሁሉ እንደ ደመኛ ጠላት መቁጠር፤ ትንሽ ልዩነት ያንፀባረቀን ሁሉ ከለየለት ተቃዋሚ ማምታታት፤ ልዩነት ማሰማትን እንደ ክተት አዋጅ ማየት...እነዚህ ሁሉ የዚህ አስከፊ ቅርስ ነፀ ብራቆች ናቸው።

በዚህ ያልተቋረጠ የወከባና የፍዳ ታሪክ በተለይ ለፖለቲካ ስልጣን ባለማቋረጥ በተካሄዱ ግጭቶች ሳቢያ ላለፉትና አንድም ጊዜ ቢሆን ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር ባላየንባቸው ሁለት ክፍለ ዘመናት ኢትዮጵያችን በተከታታይ የአስር አመታት እድሜ ሰላም ሳትታደል ቆይታለች። በዚህ ረዥም የታሪክ ዘመን ህዝባችን ያሳለፋቸው የእፎይታ ወቅቶች ቢኖሩ ተቀናቃኞቻቸውን በጦር ሜዳ አሸንፈው ስልጣን የጨበጡ ሃይሎች ህብረተሰቡን በሙሉ ያሸነፉ እየመሰላቸው እነሱም በተራቸው ወደ ታሪክ ትቢያነት እስኪወርዱ ድረስ በተሸናፊዎች ላይ የጫኑት እርቅ-አልባ ሰላም እንጂ በድርድርና በመግባባት ህብረተሰባችን በሙሉ በአሸናፊነት የወጣበት ለሁሉም የሚሆኑ የእፎይታ ወቅቶች አልነበሩም።

ዛሬ እኛ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊና አገር ወዳድ ሃይሎች ከዚህ አጥፊ አዙሪት ከጦር ድል በተገኘ ማንአህሎኝነት እንደማይወጣ ተምረን የሰላማዊ ዴሞክራሲያዊ የትግል አማራጭ አንግበን በመንቀሳቀስ ላይ ነን። በጊዜያዊ ወታደራዊ ድል ተመርኩዞ ዘላቂ ሰላምን፤ በተጭበረበረና በተድበሰበሰ የፖለቲካ ሂደት ዴሞክራሲን መገንባት እንደማይቻል ጠንቅቀን አውቀን ለነፃና ፍትሃዊ ምርጫ እውንነት ስንዋደቅ ቆይተናል። የህብረተሰቡ አንዱ ክፍል በአሸናፊነት ሌላው ክፍል ደግሞ በተሸናፊነትና በመብት አልባነት ተቆላልፈው እስከተያዙ ድረስ ሁኔታዎችን ለቀጣይ ዙር ግጭቶችና አለመረጋጋት ማመቻቸት እንደሆነ የሩቁም ሆነ የቅርቡ ታሪካችን ያረጋገጡልን ሃቅ በመሆኑ ለብሄራዊ እርቅ ስንታገል አስር አመት አስቆጥረናል።

የግንቦት 97 ዓ.ም. የምርጫ ሂደት ከኛ አልፎ ለመጭው ትውልድ ሲዘከር የሚኖርበት ዋና ምክንያት እነዚህ

የሰላማዊ ዴሞክራሲያዊ ለውጥና የብሄራዊ እርቅ እሴቶች በግንባር ቀደምነት ከተሰለፍነው ታጋዮች አልፈው በህብረተሰባችንም ሰርፀው በመግባታቸውና ህዝባችን ለዘመናት ተቆላልፈን የቆየንበትን አጥፊ አዙሪት ሰባብሮ አዲስ ምእራፍ የፈነጠቀበት የህዝባዊ ድል ሂደት መሆኑ ነው።

የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ህዝብ ድል ከነባሩ የአመፅ ፖለቲካ ባህል ተላቆ፤ በገዥው ፓርቲ የምርጫ ቦርድ ሳይሆን በራሱ ሰላማዊ ትግልና በራሱ የተባበረ ድምፅ ሃያልነት ብቻ ተማምኖ እኛን ባኮራ የውጭውን አለም ባስደነቀ መልክ የምርጫ ሂደቱ ውስጥ በሙሉ ልብ መሳተፉ ሆኖ እናገኘዋለን። ህዝባችን በዚህ መልክ ለነባሩ ባህል ጀርባ ሰጥቶ በመንቀሳቀሱ በታሪካችን ለመጀመሪያ ጊዜ በአመፅ ሳይሆን በሰላማዊ ተጋድሎ መላው አለም እየታዘበ የመንግስት ለውጥ አድርጓል። ጥቂት የኢህአዴግ መሪዎች እየተሰበረ ያለውን የጥፋት አዙሪት መልሰው ለመግጠም የህዝባችንን ድምፅ በጠራራ ፀሃይ ሰርቀው የሸፍጥ ድላቸውን ማወጃቸው ይህንን ታሪካው ሃቅ ምንም አይቀይረውም። ህዝባችን የንፁህ ልጆቹ ደም በአደባባይ እየፈሰሰም ቢሆን "በሰላማዊ ሂደትም በምርጫም ለውጥ አይቻልም" ብሉ እነሱ እንደተመኙት አስከፊ ወጥመዳቸው ውስጥ አልወደቀላቸውም።

ሁለተኛው ታሪካዊ ድል እዚህ ላይ ነው። በመስዋእትነትና በሰላማዊ ትግል ያገኘውን ድል ለማስመለስ ህዝባችን በአመፅ የተሰማሩበትን ጥቂቶች በአመፅ ሊቋቋማቸው አልተነሳም። አሁንም እንደ ቅድመ ምርጫው ዘመን በአንድነቱና በሃያልነቱ ተማምኖ አመፀኞቹን በሰላማዊ የትግል ስልት፤ ህገ ወጦቹን በህጋዊ የትግል ስትራቴጂ ለመቋቋምና ለዚህም የተጠየቀውን ማንኛውንም መስዋእትነት ለመክፈል ቁርጠኛነቱን አሳያቸው። "ስልጣን በምርጫ" ካሉ በኋላ ምርጫ ሳይቀናቸው ሲቀር ወደ ነባሩና ያረጀ ያፈጀ "ስልጣን በአመፅ" ወደሚል ስትራቴጂ ተመልሰው የተዘፈቁት እነዚህ ጥቂት ፀረ ህዝቦች ብቻ እንጂ ህብረተሰባችን አይደለም። የራሳቸውን የስልጣን ጥም ለማርካት የሚያካሂዱትን መፍጨርጨር በአጠቃላይ ለኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎች ከዚያም አልፈው ወንድም ለሆነው ለትግራይ ህዝብ የሞት ሽረት ጥያቄ አስመስለው በማቅረብ ቀቢፀ ተስፋነት ብቻ ሊሰጠው በሚችል የአጥፍቶ ጠፊ ጉልበት እየተንቀሳቀሱ የጥላቻ መርዝ ፕሮፓጋንዳቸውን ለመንዛት ላይ ታች ሲሉ አየናቸው። እዚህም ላይ ህብረተሰባችን "እንመራሃለን" ከሚሉት ጥቂት ኋላ ቀር ሃይሎች ምን ያህል ልቆ የተራመደ መሆኑን የሚያረጋግጥበት ሌላ ሶስተኛ ድል ተጎናፀፈ።

ይህ ሶስተኛው ድል ከነባሩና ከአስከፊው አዙሪት ሰብሮ በመውጣት ድል አድራጊው ህዝባችን አሁንም በታሪካችን ለመጀመሪያ ጊዜ አሸናፊዎችንም ተሸናፊዎችንም ለሚያካትት የሰላምና የዴሞክራሲ ሂደት በመቆም የብሄራዊ አንድነት የሽግግር ዘመን መንግስት እንዲቋቋም ዴሞክራሲያዊና አገር ወዳድ ልጆቹ ያቀረቡትን የቀውስ መውጫ ሃሳብ በሙሉ ልብ በመቀበሉ የተጎናፀፍነው ድል ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ ይህንን ታሪካዊ ጥሪ በመቀበል ከኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎች አልፎ ለሚያዋክቡት፤ ለሚገሉት፤ የንፁህ ልጆቹን ደም በጠራራ ፀሃይ ለሚያፈሱት፤ ለሚያንገላቱትና ለሚያዋርዱት የኢህአዴግ መሪዎችም የእርቅ እጁን በመዘርጋት በአኩሪ ታሪኩ ላይ ጠባሳ ሆኖ የቆየውን የእርቅ አልባ ድልና የአሸናፊዎች ሰላም ሂደት ለአንዴም ለዘልአለምም አንቅሮ የተፋው መሆኑን አይን ላለው ሁሉ በማያሻማ ሁኔታ አሳየ።

እነዚህ ሁሉ በትግልና በመስዋእትነት የተገኙ ድሎች በቋፍ ያሉ ድሎች ናቸው። እያከተመ ያለውን ክፍለዘመን ከነደምና እንባው አራግፈን በአዲስ መንፈስ ወደ አዲስ የኢትዮጵያ ክፍለዘመን ለመሸጋገርና የሰላም፤ የአንድነትና የብልፅግና ዘመን ለመክፈት ከተመኘን እየተሰበረ ያለው አዙሪት መልሶ ገጥሞ እንደገና በአመፅ፤ በጭቆና፤ በድህነት አዙሪት ውስጥ እንዳንዘፈቅ ከፈለግን ብዙ አማራጮች የሉንም። የጥፋት አዙሪቶቹ መልሰው መግጠም እንዳይጀምሩ የተፈለገውን መስዋእትነት ሁሉ እየከፈልን ታሪካዊ ድላችንን መንከባከብ ይገባናል። ከህዝባችን ጎን ሆነን እንንከባከበዋለን።

ይህ የኢትዮጵያ ህዝብና የታጋይ ልጆቹ ታሪካዊ ተጋድሎ "ድምፃችን ይከበር" ከሚል ቀጭን የምርጫ ውጤት ላይ ካተኮረ መፈክር እጅግ አልፎ የሚሄድ ተጋድሎ ነው። ከዚህ ዘልቀን ህብረተሰባችን ለውጥ በሰላም፤ ሰላም በእርቅ፤ እርቅ ህብረተሰቡን በሙሉ ባካተተ ድል በሚሉ አዳዲስ እሴቶች ስር ተሰልፎ የሚያካሂደው ትግል ነው። ካለፉ ካረጁና እነሱም እንደክፍለ ዘመኑ ከመሸባቸው ኋላ ቀር አስተሳሰቦችና ከነሱ አራማጆች ጋር "ድላችን

ይከበር" የሚል መፈክር አንግበን የምናካሂደው ታሪካዊ ትንንቅ ነው። በዚህ መልክ ህብረተሰባችን የተጎናፀፈውን ድል እንድንንከባከብ የሚገፋፋን ለኢትዮጵያችን ከአዲስ ክፍለ ዘመን ጋር ለአዲስ ብሩህ ተስፋ ያለን ጉጉት ብቻ አይደለም። እንደማንኛውም ገና በቋፍ ያለ ድል ይህንንም ጥቂት የስልጣን ጥመኛና ያከተመ ዘመን ሃይሎች በአመፅ እንዲፈታተኑትና እንዲቀለብሱት ከፈቀድንላቸውና ህዝባችን ታግሎና ተሰውቶ ያገኘውን ድል በሸፍጥና በአመፅ መልሶ ከተነጠቀ ሰላም፤ ዴሞክራሲ፤ ምርጫ ወዘተ በሚባሉ እሴቶች መጨረሻው ለማይታይ ረዥም ዘመን ተስፋ የሚቆርጥበትና የተገላገልናቸው የመሰለን የጥፋት አዙሪቶች ውስጥ መልሰን የምንዳክርበት አደጋም እንዳለ ጠንቅቀን ስለምናውቅም ነው።

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ህብረት (ኢዴሃህ) እና ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ (ቅንጅት) ከዚህ መሰረታዊ ሃቅ በመነሳት ህብረተሰባችን የተጎናፀፈውን ታሪካዊ ድል ላለመንጠቅ በማሳየት ላይ ካለው ወኔ የሚመጥን የአላማ ፅናት እንደሚጠበቅባቸውና በዚህ በቀውጢ ቀን ህዝባችን ከሚያንፀባርቀው የአመራር ጥማት የሚመጥን የትግል ስትራቴጂ ጥራት ወሳኝ መሆኑን በመገንዘብ ታሪክና ህዝብ ለጣለባቸው አደራ ብቁ ሆነው ለመገኘት ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ ዝግጁ መሆናቸውን ለኢትዮጵያ ህዝብ ያበስራሉ። በዚያው ልክ ደግሞ ለኢትዮጵያችን ወሳኝ በሚሆኑት በሚቀጥሉት ሳምንታትና ወራት በህዝባችን ወኔ እየተበረታታን የምንያያዘው አዲስ የትግል ምእራፍ ከፖለቲካ ድርጅቶች አልፎ በአጠቃላይ ህብረተሰቡን፤ በነጠላ ደግሞ ራሱን ወይም ራሱዋን እንደዚች አገር የቁርጥ ቀን ልጅ የሚቆጥርን የምትቆጥርን እያንዳንዱን/እያንዳንዷን የኢትዮጵያ ዜጋ የሚመለከት የታሪካዊ ትግል ምእራፍ ውስጥ ገብተናል ብለን እናምናለን።

ከዚህ በመነሳት በሁለቱ ድርጅቶች አነሳሽነት ለመጭው መስከረም 20 እና 21 1998 ዓ.ም. በህገ መንግስቱ ማእቀፍ ውስጥ የህዝባችንን ድል ለማስከበር ስለሚካሄደው ሰላማዊና ህጋዊ ቀጣይ ትግል ለመምከር የፖለቲካ ድርጅቶች፤ የተለያዩ የሙያ ማህበራት፤ የሴቶች፤ የወጣቶችና የተማሪዎች፤ የባህል፤ የሃይማኖት ስብስቦችና ተወካዮችና ከየአካባቢው የሚጋበዙ የሃገር ሽማግሌዎች የሚሳተፉበት አንድ ታላቅ " የሰላም፤ የዜጎች አንድነት፤ ትስስርና የዴሞክራሲ" አገር አቀፉ ጉባኤ እንዲጠራ በተደረገው ስምምነት መሰረት ግብረ ሃይል ተቋቁሞ ዝግጅቱን በማጠናቀቅ ላይ ይገኛል። እንደዚሁም በማግስቱ መስከረም 22 ቀን እሁድ ከአዲስ አበባ ጀምሮ በጠቅላላው በሃገሪቱ ዋና ዋና ከተሞች እንዲሁም በአለም አቀፍ ደረጃ በርካታ አገሮች"የሰላም፤ የዜጎች አንድነት፤ ትስስርና የዴሞክራሲ የድጋፍ ሰልፎች" እንዲዘጋጁ ሃሳብ ቀርቧል። በነዚህ በሃገር ውስጥም ሆነ በውጭ በሚደረጉ ሰላማዊ ሰልፎች የሃገራችን እጣ ፈንታ ያገባናል የሚሉ ዜጎች በያሉበት በነቂስ ወጥተው የህዝባችን ታሪካዊ ድል እንዲከበር ለሚደረገው ታሪካዊ ተጋድሎ ያላቸውን ድጋፍ ለመግለፅ እንዲዘጋጁ አገራዊ ጥሪያችንን እናስተላልፍላቸዋለን።